ልጆች - ፍቅሮች - ተሰፋዎች - አልማዞች - እንቁዎች - ጌጦች!
ልጆች - ለምለሞች - ደስታዎች
ልጆች ውቦች - ቆንጆዎች
ልጆች - አበባዎች
ልጆች -ሚያምሩ - ፈርጦች!
ዩሚያበሩ - ብርሃኖች
ልጆች - ወርቆች
ልጆች የመንፈስ - ሀብሎች
ልጆች የማህጸን - ጽጌረዳዎች!
ልጆች እጅግ በጣም ጥሩዎች
ልጆች የኑሮ - ዓይኖች!

ልጆች እንደምን አላችሁ?
ደህና ናችሁ? እኛ ደህና ነን።

እንኳን ለአዲሱ ዓመት ለቅዱስ የኋንስ በሰላም ከባቢ እና ከማሚ ጋር አደረሳችሁ

እን ቁ ጣ ጣ ጣ ሽ ------ ልጆች

እንኳን መጣሽ አላችሁ ....

በሉና እኔ ሥርጉተ፣ መክሊት ከአብ እና አርትህ ከአብ ሰላም እያልናችሁ እኮ ነው!

አዎን ልጆች አዲሱ አመት የደስታ የፍቅር እንዲሆን ከልብ እንመኝላችሁ አለን፡

..... 2

# አድዮ አበባ እና ቅዱስ የኋንስ

*******

ልጆች .... ቅዱስ የኋንስ የዘመን መለወጫ ነው። ቅዱስ የኋንስ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚመጣው።

ቅዱስ የኋንስ የሚውለው መስከረም አንድ ቀን ነው። በሐገራችን በኢትዮጵያ መስከረም የወራቶች ሁሉ መጀመሪያ ነው።

ቅዱስ የኋንስ በጣም የሚወደድ በዓል ነው። ለልጆች አዲስ ልብስ ይገዛል። ጫማ ይገዛል። በግ ይተረዳል።

ደሮ የታረዳል። ቤተሰቡ ጎረቤቱ በሙሉ በደስታ አብሮ በመብላት እና በመጠጣት በጋራ በደስታ ያሳልፋሉ።

ልጆች ደግሞ ምን ያደርጉ መሰላችሁ? አባባ ይሰሩ እና ለባቢ፣ ለማሚ፣ ደግሞ ለሚወዷቸው ሁሉ ጥዋት ይነሱ እና እንቁጣጣሽ ይላሉ። ወላጆች በበኩላቸው ደግሞ ገዝተው ግን ሸሽገው ያስቀመጡትን ስጦታ ለልጆች ይሰጣሉ።

ልጆች ለመሆኑ ማሚ እና ባቢ አዲስ ልብስ እና ጫማ ገዙላችሁ?!

ልጆች ... ኢትዮጵያ እናት ሐገራችን እኮ ሌሎች ሐገሮች የሌላቸው በጣም ደስ የሚል ባህል ያለት ቆምጆዬ ሐገር ናት።

ውይ ልጆች ሳልነገራችሁ .... አንድ አበባ አለች ከአለ ቅዱስ የኋንስ የመትበቅል። ማን ትባላላች?!

<u>አድዮ አባበ።</u> ብሄራዊ አበባ ትባላለች። ወላጆች ብሄራዊ ማለት ምን ማለት እንደሆን እባካችሁ ለልጆች ንገሩልን እናመሰግናለን።

አድዮ ቢጫ ናት። ታዲያ በሁሉም ቦታ ተገኛለች። ለዚህ ነው አድዮ ብሄራዊ አበባ የተባለችው። በሰከረም አንድ ሜዳው ተራራው ወንዙ ሰፈሩ ሁሉ ልበስ አለው በቅዱስ የኋንስ። የምን?! የአድዮ አበባ። ....

ልጆች እናንተስ አድዮ አይደላችሁ - የህይወት - የነፍስ - የደስታ የፍቅር አባባዎች መስከረሞች!!!!

መልካም አዲሰ ዓመት ፍቅሮቻችን!

እግዜብሄር አምላክ ያሳድግልን